# "የዲሲው "አርበኛ"

"አርበኛ"ነዐምን በግንቦት ሰባት ፓልቶክ ሩም(ecadf)ውስጥ በፀረ አማራዋ ብዙ ወንድምአግኘሁ(ሙያዬ) የተደረገለት ኢንተርቪው ላይ ብዙውን ሰአት ያሳለፈው እንደተለመደው ስለ ሻቢያ ቅዱስነትና ብቸኛ የኢትዮጵያ አለኝታነት በመስበክ ነበር፤ሌላው የታዘብነው ነገር፤ስለራሱ ድርጅት ያለው በጣም የተለጠጠና የሌሎችን ድርጅቶች ህልውና ፍጹም የካደ ግምት ሲሆን ሌላውና አስገራሚው የኔን ትኩረት የሳበው ጉዳይ ስለግንቦት ሰባት አመራር የዘር ስብጥር ጠይቃው የሰጠው መልስ የሚገርም ከመሆኑም በላይ ጥያቄው ሆን ተብሎ ሞረሽ ወገኔን ጥላሸት ለመቀባት ታስቦና ተቀነባብሮ የቀረበ ለመሆኑ ለመገዘብ ችለናል።ለማንኛውም የመጨረሻውን ሴትዬዋ የጠየቀችውንና እሱ የሰጠውን መልስ አደምጡት።

"እነሱ ምን ያርጉ ከኛ ሰው ሲታጣ"አለ ፋሲል ደሞዝ፤እኛው የአማራው ልጆች ነን ራሳችንን ዝቅ አድርገን የማንም ኩታራ እንዲጎትተን የፈቀድንለት፣ቢንቁን አይፈረድባቸውም።አሮሞዎቹ የሚከበሩት በራሳቸው ዙሪያ ተሰባስበው ራሳቸውን ስላስከበሩ ነው ሰውን ሁሉ በየአዳራሹ ቁጭ ብድግ የሚያረጉት፤የአማራው ልጆች የራሳቸው ድስት አሮባቸው ለሌሎች ሲያማስሉ የማታ ማታ ውርደት ሆነ ዋጋቸው።

ለማንኛውም ለነ"አርበኛ" ነአምን ዘለቀና ተላላኪዎቻቸው(ECADF)የምንለው ነገር ቢኖር ዛሬ የአማራው ልጆች ትላንት እናንተ ስትጎቱቷቸው የነበሩ አይናቸውንም ሆነ ጆራቸውን ከፍተው ተመልክተው የራሳቸውን ግንዛቤ ወስደው ድምዳሜ ላይ የመድረስ ብቃታቸውን ስላጎለበቱ ከንግዲህ በናንተ ጓዳ ውስጥ በሚፈበረክ የውሸት ናዳ አይምሯቸው እንደማይበወዝ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።"ነቅተናል፤አይናችንን ከፍተናል"ከንግዲህ አንሸወድም።ቅድሚያ ለራሳችን።

ሞረሽ ወገኔ የቤት ስራውን የጨረሰ ይመስለኛል፤እነ"አርበኛ"ብርሃኑ ነጋና እንደ ነዐምን ዘለቀ አይነቶቹ የአማራውን ልጅ አይኑንና ጆሮውን ጋርደውበት የነበረውን
ጥቁር መጋረጃ ቀዳዶ በመጣል እንዲያዩና እንዲሰሙ አድርጓቸዋል።

ስለሆነም፤የዋሽንግተኑ "አርበኛ"ነዓምን ዘለቀ ለካደው የግንቦት ሰባት አመራር ከአማራ የጠራ ስብስብንት ጉዳይ እሱ ያለንውን ሳይሆን የአማራው ልጆች በራሳቸው አነሳሽነት ተነሳስተው ውነቱን ከውሸት የማጥራት የምርምር ሂደት ውስጥ በደረሱበት ውጤት ላይ ተመርኩዘው እንጂ በማንም ተሞልተው አይደለም፤ከንግዲህ ወደፊት የሚሆነውም ይኸው ነው።
"አርበኛ"ነዓምን ያለውን ብሏል፤የአማራ ልጆች ደግሞ ሁሉንም ነገር አብጠርጥረው ስለሚያውቁ ስለግለሰቡ ይበልጥ ግንዛቤ ጨብጠዋል።
"ድፍርስና እውነት እያደር ይጠራል"እድሜ ብቻ ይስጠን። አሜን!!!!

የግንቦት ሰባት አመራር የስም ዝርዝር ደግመን ደጋግመን ቋቅ እስኪላችሁ እንለጥፋለን።በነገራችን ላይ የግንቦት ሰባት የሴንትራል ኮሚቴው ብቻ አይደለም ከአማራ የጠራው አመራር፤በየአህጉሩና አገራት ያሉ የድርጅቱ ተወካዮች 90% ከአማራ የጸዱ ናቸው።
ይህንን ስንል ደግሞ ባልቴቷ አርበኛ ሙሉ ወንድማገኝ እንዳለችው አሉባልታ ሳይሆን ሁላችሁም የአማራ ልጆች በየአካባቢያችሁ ያሉትን የግንቦት ሰባት ተጠሪዎች ብታጠኗቸው የምትገረሙበት ጉዳይ ነው።"ለማያውቅሽ ታጠኚ"አለ ያገሬ ሰው።
እንተዋወቃለን ጓድ የዋሽንግተኑ"አርበኛ"I was there.
ከአማራው የተጣላ መቅኖ የለውም
በአማራው ላይ የሚሰራ ደባ ለኢትዮጵያም አይበጅም
አማራን አግልላችሁ የትም አትደርሱም፤መዳረሻችሁ ገደል ነው።

ሰለሞን አብራ